**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**

סוג הבחינה: א. בגרות לבתי ספר על־יסודיים
ב. בגרות לנבחנים אקסטרניים
מועד הבחינה: קיץ תשע"ב, 2012
מספר השאלון: 572301, 153

# אמהרית

שלוש יחידות לימוד

## הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה: בשאלון זה ארבעה פרקים.

| | | |
|---|---|---|
| פרק ראשון | — | 30 נקודות |
| פרק שני | — | 25 נקודות |
| פרק שלישי | — | 30 נקודות |
| פרק רביעי | — | 15 נקודות |
| סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש: אין.

ד. הוראות מיוחדות:
(1) כְּתוֹב את כל התשובות בשאלון עצמו (במקומות המתאימים).
(2) כְּתוֹב את כל התשובות בעט בלבד. אסור למחוק בטיפקס.
(3) בסיום הבחינה החזר את השאלון למשגיח.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

/המשך מעבר לדף/

| አስተውል! መልሶችህን በግልፅና በትልልቅ ፊደሎች በእስክርቢቶ ብቻ ጻፍ። | שים לב: את התשובות כְּתוֹב בָּרוּר, בְּעֵט (ולא בעיפרון) ובאותיות גדולות. |
|---|---|

## **ክፍል አንድ** (30 ነጥብ)

ከታች የተሰጠውን የተማርከውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልስ።

## **פרק ראשון** (30 נקודות)

לפניך קטע שנלמד.
קרא את הקטע, וענה על כל השאלות 1-10 שאחריו.

## አንበሳና ዘጠኝ ጅቦች

ዘጠኝ ጅቦች ከአባታቸው ጋር ይኖሩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በጣም ራባቸው። ምክንያቱም ለሁለት ቀናት ያህል ምግብ ስላላገኙ ነው። ከረሃቡ የተነሳ በጣም ደክሟቸው ስለነበር ከአንድ ትልቅ ዋርካ ሥር አረፉ።

በዚያን ጊዜ አንድ አንበሳ ለአደን በዚያ ሲያልፍ፥ ጅቦቹ "አያ አንበሳ! ርቦናልና መላ ፈልግልን" አሉት። "ኑ ወደጫካ ሄደን እንስሳትን እናድን" አላቸው። ጅቦቹም በአንበሳው ሐሳብ ተስማምተው አብረው ወደጫካ ሄዱ።

ወደጫካ ሲሄዱ በመንገድ ላይ አሥር በሬዎች በማየታቸው በጣም ደስ አላቸው። ከዚያም አሥሩንም በሬዎች ይዘው ወደአንበሳው ቤት ሄዱ። አንበሳውም ዘጠኝ ድልብ በሬዎችን ለራሱ ወስዶ አንድ ኮሳሳ በሬ ለጅቦቹ ሰጣቸው። ዘጠኙም ጅቦች የተሰጣቸውን ኮሳሳ በሬ ይዘው ወደሽማግሌው አባታቸው ጋ ሄዱ። አባታቸውም የት እንደዋሉ ቢጠይቃቸው ጉዳዩን ዘርዝረው ነገሩት። አባታቸውም በጣም ተናደደና "እንዴት ዘጠኝ ድልብ በሬዎች ለአንድ አንበሳ ሰጥታችሁ አንድ ኮሳሳ በሬ ይዛችሁ ትመጣላችሁ? እኔ ይህን ኮሳሳ በሬ ሰጥቼው ዘጠኙን ድልብ በሬዎች ባላስመልስ ወንድ አይደለሁም" ብሎ ፎከረ።

ከዚያም ዘጠኙ ጅቦች ከሽማግሌው አባታቸው ጋር በሬውን ይዘው ወደአንበሳው ቤት ሄዱ። አንበሳውም ጅቦቹን ሲያይ ተናደደና ሦስት ጊዜ አገሳ። ጅቦቹም ከፍርሃት የተነሳ ተንቀጠቀጡ። አንበሳውም ሽማግሌውን ጅብ ለምን እንደመጡ ጠየቀው። ጅቡም "አይ ለምን ዘጠኙን በሬዎች ብቻ? ይህን በሬ ጨምራችሁ ለምን ለአያ አንበሳ አልሰጣችሁም ብዬ ነው በሬውን ልንሰጥዎት ያመጣነው" አለው። አንበሳውም በሬውን ተቀብሎ ጅቦቹ ምንም ሳይዙ ባዶ እጃቸውን ወደቤታቸው ተመለሱ።

/המשך בעמוד 3/

**ጥያቄዎች** (30 ነጥብ)

በምንባቡ መሠረት ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።
(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 3 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 30 ነጥብ።)

**השאלות** (30 נקודות)

ענה על השאלות 10-1 באמהרית, לפי הקטע שקראת.
(לכל תשובה נכונה — 3 נקודות;
סה"כ — 30 נקודות)

1. ጅቦቹ በጣም የራባቸው በምን ምክንያት ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

2. ጅቦቹ ለምንድን ነው ከትልቁ ዋርካ ሥር ያረፉት?

______________________________

______________________________

______________________________

3. አንበሳው ለአደን በዚያ ሲያልፍ ጅቦቹ ምን አሉት?

______________________________

______________________________

______________________________

4. ጅቦቹ በአንበሳው ሐሳብ ተስማምተው ምን አደረጉ?

______________________________

______________________________

______________________________

5. አንበሳውና ጅቦቹ በጣም ደስ ያላቸው በምን ምክንያት ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

6. ዘጠኙ ጅቦች የተሰጣቸውን ኮሳሳ በሬ ይዘው ወዴት ሄዱ?

______________________________

______________________________

______________________________

/המשך בעמוד 4/

7. ሽማግሌው ጅብ ምን ብሎ ፎከረ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8. አንበሳው የተናደደው በምን ምክንያት ነው? ምንስ አደረገ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

9. ጅቦቹ ለምን ተንቀጠቀጡ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

10. አንበሳው ሽማግሌውን ጅብ ለምን እንደመጡ ሲጠይቀው ጅቡ ምን መለሰ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

/המשך בעמוד 5/

**ክፍል ሁለት** (25 ነጥብ)

ከታች በክፍል ያልተማርከው ምንባብ አለ የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ11-20 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ።

**פרק שני** (25 נקודות)

לפניך קטע שלא נלמד.

קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 11-20 שאחריו בעברית או באמהרית.

## አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ተብላ ትጠራለች። አዲስ አበባ የተመሠረተችው በ1887 ዓ.ም ነው። ከተማዋን የመሠረቷት የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ናቸው። ከተማዋ ከባሕር ጠለል በላይ 2440 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች። የአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብ ብዛት ወደ 3 ሚሊዮን አካባቢ ነው። በከተማዋ ውስጥ የተለያዩ አዳዲስ እና የቆዩ ሠፈሮች አሉ። ከቆዩት ሠፈሮች ውስጥ ለምሳሌ መርካቶ፣ ፒያሳ፣ ካዛንችስ፣ ቦሌ፣ ሾላ ወዘተ ናቸው። አዲስ ከተመሠረቱት ውስጥ ደግሞ ሲ ኤም ሲ፣ ላፍቶ፣ ገርጂ፣ ጉርድ ሾላ የሚባሉት ይገኛሉ። መርካቶ ዋናው የመገበያያ ቦታ ሲሆን በአፍሪካ ውስጥ ትልቁ ክፍት የገበያ ቦታ ነው። ቦሌ እና ሲ. ኤም. ሲ. ጥራት ካላቸው ሠፈሮች ውስጥ የሚመደቡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ኤምባሲዎች (שגרירויות) ቦሌ ሰፈር ይገኛሉ።

የግል መኪና የሌለው እና በሕዝብ ትራንስፖርት መጓጓዝ የሚፈልግ ሰው በከተማ አውቶቡስ ወይም በታክሲ ይጓጓዛል። የተለያዩ ዓይነት ታክሲዎች አሉ፦ እነሱም ትንሿ ታክሲ፣ ሚኒ ባስ እና ውይይት የሚባሉት ናቸው። ውይይት የሚባለው ታክሲ በአጠቃላይ 12 ሰዎችን የሚያሳፍር ሲሆን 2 ከሾፌሩ ጎን 10 ሰዎችን ደግሞ ከኋላ ይይዛል። ውይይት የተባለበትም ምክንያት ከኋላ የሚቀመጡት 10 ተሳፋሪዎች በአንድ ወገን 5 በሌላው ወገን ደግሞ 5 ተቀምጠው ፊት ለፊት የሚተያዩ ስለሆነ ነው ይባላል።

/המשך בעמוד 6/

**ጥያቄዎች** (25 ነጥብ)

በምንባቡ መሠረት ከ11-20 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ።
(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 2.5 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 25 ነጥብ።)

**השאלות** (25 נקודות)

ענה על השאלות 11-20 בעברית או באמהרית, לפי הקטע שקראת.
(לכל תשובה נכונה — 2.5 נקודות;
סה"כ — 25 נקודות)

11. የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ መቼ ተመሠረተች?

12. አዲስ አበባን ማን መሠረታት?

13. አዲስ አበባ ከባሕር ጠለል በላይ በስንት ከፍታ ላይ ትገኛለች?

14. ስለመርካቶ የምታውቀውን በአጭሩ ጻፍ?

15. ከቀዩት የአዲስ አበባ ሠፈሮች ውስጥ ቢያንስ 4ቱን ጻፍ?

/המשך בעמוד 7/

16. አዲስ ከተመሠረቱት የአዲስ አበባ ሠፈሮች ውስጥ ቢያንስ 3 ጻፍ?

17. በቦሌ ሰፈር ምን ይገኛል?

18. በከተማ አውቶቡስ እና በታክሲ የሚጓጓዘው ማን እና ማን ነው?

19. ከአዲስ አበባ የታክሲ ዓይነቶች ሦስቱን ጥቀስ?

20. ውይይት የሚባለው ታክሲ ለምን ውይይት እንደተባለ ግለጽ?

/המשך בעמוד 8/

**ክፍል ሦስት** (30 ነጥብ)

የሚከተለው ምንባብ በክፍል ውስጥ የተማርከው ነው። ምንባቡን ካነበብክ በኋላ ከ21-27 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ።

**פרק שלישי** (30 נקודות)

לפניך קטע שנלמד.
קרא אותו, וענה על השאלות 27-21 שאחריו בעברית או באמהרית.

## የካራቫን ኑሮ

እኔና ቤተሰቤ ኢየሩሳሌም ለመድረስ የነበረን ሕልም ተሳክቶልን በ1991 ዓ.ም እስራኤል ሀገር ገባን። ከዚያም አዲስ ገቢዎችን ለመቀበል ወደተዘጋጀው ካራቫን ወደሚባለው ቤት ተወሰድን። በመጀመሪያ የተለያዩ የጤና ምርመራዎች ተደረጉልን። በሁለተኛ ደረጃ የመጣነው አዲስ ገቢዎች በሙሉ የዕብራይስጥ ቋንቋ ትምህርት ጀመርን። ከቋንቋው ትምህርት በተጨማሪ በእስራኤል ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎች ጎበኘን።

ወደካራቫኑ በገባንበት ጊዜ መኝታው፣ ማብሰያው፣ መፀዳጃ ቤቱና መታጠቢያው የተሟላ መሆኑን አየን። በተቃራኒው እኔና ቤተሰቤ ስንኖር የነበረው በደሳሳ ጎጆ ነበር። ሚስቴ ውሃ የምትቀዳው ትልቅ ገንቦ ተሸክማ የግማሽ ሰዓት መንገድ ተጉዛ ነበር። የማገዶ እንጨት ለመፈለግም ብዙ ጊዜ ታጠፋ ነበር።

ሆኖም ካራቫኑ ዱሮ ከነበረን ቤት የተሻለ ቢመስልም ችግሮችም ነበሩት። በበጋ ወራት ከካራቫኑ ጣራ ዝቅተኛነት እና ከፀሐይዋ ሙቀት ኃይለኝነት የተነሳ ካራቫኑ በጣም ይሞቃል። ከመሞቁም የተነሳ ሌሊት እንቅልፍ አይወስደንም ነበር። ካራቫኖቹ የነበሩባቸው አንዳንድ ቦታዎች ከከተማ የራቁ ስለነበሩ የትራንስፖርት ችግሮችም ነበሩ። ቢሆንም የካራቫን ኑሮ የሀገሪቱን ባሕል፣ ቋንቋ፣ እና የኑሮ ሥርዓት ቀስ በቀስ እንድንማር ረድቶናል።

/המשך בעמוד 9/

**<u>ጥያቄዎች</u>** (30 ነጥብ)

**በምንባቡ መሠረት ከ21-26 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ <u>ወይም</u> በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ጥያቄ የያዘው ነጥብ በጥያቄው መጨረሻ ላይ ተጽፏል።)**

**<u>השאלות</u>** (30 נקודות)

ענה על כל השאלות 26-21 בעברית <u>או</u> באמהרית, לפי הקטע.
(מספר הנקודות לכל שאלה רשום בסופה.)

21. **አዲስ ገቢውና ቤተሰቡ የነበራቸው ሕልም ምን ነበር?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(3 **ነጥብ**)

22. **አዲስ ገቢዎቹ ወደካራቫን ተወስደው በመጀመሪያ ምን ተደረገላቸው?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(3 **ነጥብ**)

23. **አዲስ ገቢዎቹ ከቋንቋው ትምህርት በተጨማሪ ምን አደረጉ?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(4 **ነጥብ**)

24. **አዲስ ገቢዎቹ ወደካራቫኑ በገቡ ጊዜ ምን አዩ?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(4 **ነጥብ**)

25. **የአዲስ ገቢው ሚስት ምን ለመፈለግ ነበር ብዙ ጊዜ የምታጠፋው?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(3 **ነጥብ**)

26. **የካራቫን ኑሮ የሀገሪቱን ምን ምን እንዲማሩ ነው የረዳቸው?**

____________________________________________________

____________________________________________________

(3 **ነጥብ**)

/המשך בעמוד 10/

በትእዛዙ መሠረት 27ኛውን ጥያቄ መልስ።

ענה על <u>שאלה 27</u>, לפי ההוראות.

27. በጥያቄ 27 ከሀ-ሠ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበብክ በኋላ በምንባቡ መሠረት <u>እውነት</u> ወይም <u>ውሸት</u> በማለት ትክክለኛውን መልስ ክበብ። እያንዳንዱ (ትክክለኛ መልስ 2 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 10 ነጥብ)

27. <u>בכל אחד</u> מהסעיפים ***ሀ-ሠ***, הקף במעגל את התשובה הנכונה: **נכון** או **לא נכון**, לפי הקטע שקראת. (לכל תשובה נכונה — 2 נקודות; סה"כ — 10 נקודות)

ሀ. አዲስ ገቢዎቹ እስራኤል ሀገር የገቡት በ1984 ዓ.ም ነው። እውነት ውሸት

ለ. በሁለተኛ ደረጃ አዲስ ገቢዎቹ በሙሉ የዕብራይስጥ ቋንቋ ትምህርት ጀመሩ። እውነት ውሸት

ሐ. ከካራቫን በፊት አዲስ ገቢውና ቤተሰቡ ይኖሩ የነበረው በቪላ ቤት ነበር። እውነት ውሸት

መ. ካራቫኑ ከመሞቁ የተነሳ ሌሊት እንቅልፍ አይወስዳቸውም ነበር። እውነት ውሸት

ሠ. ካራቫኖቹ በነበሩባቸው ቦታዎች ሁሉ የትራንስፖርት ችግሮች አልነበሩም ። እውነት ውሸት

/המשך בעמוד 11/

**ክፍል አራት** (15 ነጥብ)

የሚከተለው ምንባብ በክፍል የተማርከው ነው።

ምንባቡን ካነበብክ በኋላ ከ28-35 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።

**פרק רביעי** (15 נקודות)

לפניך קטע שנלמד.

קרא את הקטע, וענה על כל השאלות 35-28 שאחריו באמהרית.

## ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ

አፄ ቴዎድሮስ እ.አ.አ በ1818 ዓ.ም ተወለዱ። የተወለዱትም ከጎንደር ከተማ 12 ኪ.ሜ ርቃ በምትገኘው ዳዋ በምትባል የገጠር መንደር ነው። የቴዎድሮስ አባት አቶ ኃይሉ የተወለዱት ቋራ ሲሆን እናታቸው ወይዘሮ አትጠገብ ደግሞ እንፍራንዝ በሚባል ቦታ ነው።

አፄ ቴዎድሮስ ከ1855-1868 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን በንጉሥነት አስተዳድረዋል። ኢትዮጵያን ባስተዳደሩበት ጊዜ ከውጭ የሚመጡ ጠላቶች አገሪቱን እንዳይወሩ ሲዋጉ ቆይተዋል።

በ1868 የጦር ኃይል ትብብር ለማድረግ ለእንግሊዝ ጥያቄ አቀረቡ። ነገር ግን እንግሊዞች ጥያቄውን አልተቀበሉም። በዚያ ምክንያት ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች ሰብስበው አሰሩ። ከዚያም በዘመናዊ መሣሪያ የታጀበው የእንግሊዝ የጦር ኃይል ከቴዎድሮስ ወታደሮች ጋር ተዋግቶ ብዙ ወታደሮች ሞቱ። ከዚያም የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርጎ በ24 ሰዓት ውስጥ ቴዎድሮስ እጅ እንዲሰጡ ተጠየቁ። "ኃይለኞችን እንደ ሕፃን በክንዱ ይዞ የኖረ እንደ እኔ ያለ ወታደር ዛሬ በሰው ክንድ መያዝ አይፈልግም" ብለው መልስ ሰጡ። ከዚያም በራሳቸው ሽጉጥ እራሳቸውን አጠፉ።

/המשך בעמוד 12/

**ጥያቄዎች** (15 ነጥብ)
ከ28-35 ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ
መሠረት በአማርኛ ብቻ መልስ።
(እያንዳንዱ ጥያቄ የያዘው ነጥብ በጥያቄው
መጨረሻ ላይ ተጽፏል።)

**השאלות** (15 נקודות)
ענה על השאלות 28-35 באמהרית,
לפי הקטע שקראת.
(מספר הנקודות לכל שאלה רשום בסופה.)

28. አፄ ቴዎድሮስ መቼ ተወለዱ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

(1 ነጥብ)

29. አፄ ቴዎድሮስ ማን በምትባል መንደር ተወለዱ? መንደሯስ ከጎንደር ምን ያህል ትርቃለች?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

(2 ነጥብ)

30. የአፄ ቴዎድሮስ አባት ማን ይባላሉ? የተወለዱትስ የት ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

(2 ነጥብ)

31. ኢትዮጵያን ባስተዳደሩበት ጊዜ ምን ሲያደርጉ ቆይተዋል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

(2 ነጥብ)

/המשך בעמוד 13/

32. አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዞች ጥያቄ ያቀረቡት ምን ለማድረግ ነበር?

(2 ነጥብ)

33. እንግሊዞች ጥያቄውን ባለመቀበላቸው ቴዎድሮስ ምን አደረጉ?

(2 ነጥብ)

34. የተኩስ አቁም ስምምነት ከተደረገ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ምን ተጠየቁ።

(2 ነጥብ)

35. አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዞች የሰጡት መልስ ምን የሚል ነበር?

(2 ነጥብ)

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך